# የሄፐታይተስ ቢ ምርመራ ያድርጉ

ሄፓታይተስ ቢ ጉበትን የሚያጠቃ ቫይረስ ነው። ሄፓታይተስ ቢ የጉበት ካንሰር ሊያስከትል ይችላል፣ ነገር ግን ጉበትዎን ጤናማ ለማድረግ የሚያግዙ ሕክምናዎች አሉ።

የሄፐታይተስ ቢ በሽታ ያለባቸው ሰዎች ብዙውን ጊዜ ምንም አይነት የሕመም ምልክት አይታይባቸውም፤ ነገር ግን በሽታውን ወደ ሌሎች ሰዎች ሊያስተላልፉ ይችላሉ።

ሄፓታይተስ ቢ ለመከላከል የሚያስችል ደህንነቱ የተጠበቀ እና ውጤታማ ክትባት አለ።

## ሄፓታይተስ ቢ በሚከተሉት መንገዶች ይተላለፋል፥

- በወሊድ ወቅት ከእናት ወደ ልጅ
- ሄፐታይተስ ቢ ካለበት ሰው ጋር የደም ንክኪ ሲፈጠር
- ወሲባዊ ግንኙነት
- እንደ ምላጭ፣ የጥርስ ብሩሽ ወይም የጥፍር መቁረጫ ያሉ የግል ንጽህና መጠበቂያ እቃዎችን ማጋራት

## ሄፓታይተስ ቢ በሚከተሉት መንገዶች አይተላለፍም፥

- ምግብ ወይም የመመገቢያ ዕቃዎችን ማጋራት
- እንደ መተቃቀፍ፣ መሳሳም ወይም እጅ ለእጅ መያያዝ ያሉ የተለመዱ ንክኪዎች
- ውሃ ወይም አየር

## ለሄፐታይተስ ቢ ምርመራ ማድረግ ያለበት ማን ነው፥

- እርጉዝ ሴቶች
- ሄፓታይተስ ቢ ካለበት ሰው ጋር የሚኖሩ ሰዎች
- ሄፓታይተስ ቢ በብዛት በሚከሰትባቸው አካባቢዎች የተወለዱ ሰዎች ለምሳሌ አፍሪካ ወይም እስያ
- ወላጆቻቸው በብዛት ሄፓታይተስ ቢ ከሚገኝባቸው አካባቢ የመጡ ሰዎች፤ ለምሳሌ አፍሪካ ወይም እስያ

DEPARTMENT OF HEALTH
PO Box 64975, St. Paul, MN 55164
651-201-5414 or 1-877-676-5414
www.health.state.mn.us/hepatitis
4/2026